ለዚህም ነው የሥቃዩን ጊዜ ለማሳጠር ሁላችንም ቆርጠንና አብረን እንታገል የምንለው:: ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ለህዝቧ የነፃነትና የብልፅግና፣ የእኩልነትና የእድገት ሀገር እንድትሆን ዛሬም ህዝባዊ ተጋድሎን ማፋፋምና ማጠናከር የሚያስፈልገው:: በዚህ አውሬ መንግሥት ስርዓት የረሀብና የእልቂት ደመና የተሸፈነችው የነፃነት ጨረቃ ብርሃኗን በኢትዮጵያ እንድትፈነጥቅ ለማድረግ ብዙ ሺህ ህፃናት በረሀብ ጣረሞት አለዕድሜአቸው ገርጅፈው የሚረግፉበትን፣ አያሌ ሀገር ወዳዶች በጠራራ ፀሐይ ሆነ በሌሊት ውድቀት የሚታረዱበትን፣ ሰው በሃገሩ በፍርሃትና በሽብር የሚሸማቀቅበትን፣ በሚሊዮን ሀገሩን ጥሎ ለስደት የሚዳርግበትን፣ ሀገር የጥቂት ሰው በሊያቸና የወራሪዎች መፈንጪ የምትሆንበትን ሁኔታ ለማጥፋትና የነፃነትን ቀን ለማምጣት ከትግል ሌላ ምንም አማራጭ የለንም:: ጦርነትን የሚያጠፋ ጦርነት ማካሄድ፣ መከራን ለማጥፋት መሰቃየት፣ ረሀብን ለማጥፋት ረሀብን መቅመስ ጭፍጨፋን ለማጥፋት መስዋዕትነትን መክፈል ..... ይህ ነው የትግል ትርጉሙ:: ይህ ነው ለሀገር ቤዛ የሚሆነው መንገድ::

የፋሽስት መንግሥትና የሶሻል-ኢምፔሪያሊዝም
ፀረ-ሕዝብ አገዛዝ በተባበረ የሰፊው ሕዝብ ክንድ ይደቃል!!

ለፋሽስት ጭቆና መልሳችን አሁንም ትግል ነው!!

እ ና ቸ ን ፋ ለ ን !!!